## የቆሮንቶሱ ድል

እንደዛው እንደጥንቱ፣
ቢያይልበት ክፋቱ፣
ትዝ ቢለው ማሳሳቱ፣
ሔዋንን ማስወጣቱ፣
ገነትን ማሳጣቱ፣
አዳምን ማሳደዱ ከሚወደው ቤቱ፣
ተፈርዶበት ጥሮ ግሮ እንዲበላ በጉልበቱ፣
አልበቃ ቢለው የአዳም ሞቱ፣
ዛሬ መጣ ለሽንፈቱ።

የዓለም ንጉሥ ዳግማዊው አዳም፣
ሲገሰግስ ወደ ገዳም
አጅሬ ዲያብሎስ መቼ አፈረና
ተከትሎት አብሮ አቀና
ሊጥለው በፈተና።

ለምዶ ኖሮ ሰው ሲገዛ
አስመስሎ እያዋዛ
ኋላ ሲጥል እንደዋዛ።

በትዕቢት አስወጥሮ
ለብቻ አስከብሮ
ሌላን ጥሎ ለራስ አድሮ
መራራ ሞትን በጎን ቀጥሮ
መስሎት ነበር የሚሠራ
የሚጠቅም ትዕቢት ጉራ
ግን ተመታ በሕይወት እንጀራ።

ድል ቢነሳ በትዕቢቱ
ዳግም መጣ በስስቱ
ጌታን ሊጥል በምትሃቱ
ድንጋዩን ወደ እንጀራ
ለውጥና ተአምር ሥራ
ብሎ አዘዘው መስሎት ተራ።

የዓለም ንጉሥ ክፉን ቀጪ

ጠብን አጥፊ ሰላም አምጪ
ቃሉ ምግብ ሕይወት ሰጪ
ዲያብሎስን ጣለው ወደ ውጪ።

ለሦስተኛ ጊዜ በዚያ በበረሃ
ሲያወጣ ሲያወርድ ሲያሰላስል
መግደያ ዘዴን ሲያብሰለስል፤

ዓለሙን የጣለበት
አንዱን ከአንዱ የለየበት፤

ገንዘብን አስነክሶ
ስብዕናን አስረክሶ
የመርገምን ጨርቅ አስለብሶ፤

ሊያሰግድ ሊያስደገድግ
ከአንዱ ነጥቆ ሌላ ሲያሳድግ
መልሶ ሞቱን ሲሻ ሲፈልግ
የሚሰጠውን ደስታ ፈንጠዝያ
መልካሙን ሰው የለየበት ከአምላክ ጉያ

ለጥርስ ማፋጨት የዳረገበት
ፍጥረታትን የጣለበት
መላእክትን ሳይቀር ያስቆጣበት

ያ! እኩይ ሥራው

በቆሮንቶስ ገዳም መቼ ቦታ አግኝቶ
ይኸው ሲሄድ ታየ ውርደቱን ሸምቶ
ዳግም ላይመለስ ላይቀርብ ተገዝቶ
አንተ ሰይጣን ተብሎ በአምላክ ተጠርቶ
ባመጣው ፈተና በሶስቱም ተረትቶ።

ኃይለ መስቀል ተስፋዬ (ለንደን)
መጋቢት 1996